መልእክት ሰባት

**በእግዚአብሔር ንግሥና እና ራስነት ሥር**
**እግዚአብሔር የወሰነውን ሥርዓት ለመጠበቅ**
**እና እስራኤልን ሁሉ ወደ ትክክለኛ ስርአት ለማምጣት**
**እግዚአብሔር ሴት ለወንድ መገዛቷን በተግባር የተለማመደችውን**
**ዲቦራን የእስራኤል ፈራጅ**
**እና በእስራኤል ያለች እናት አድርጎ ማስነሣቱ**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፡- *መሣ*. 4—5

I. ***የመሣፍንት መጽሐፍ እስራኤል ንጉሣቸው የሆነውን እግዚአብሔርን በመግፋት እንደበደለው ያሳየናል፤ እግዚአብሔርን እንደ ንጉሣችን፣ እንደ ጌታችን፣ እንደ ራሳችን እና እንደ ባላችን ከተውነው በእግዚአብሔር እይታ ይህ በጣም ክፉ መሆን እና ታላቅ ክፋት ነው—1 ሳሙ. 8፡7፤ 12፡17፤ 19፤ መሣ. 21፡25፤ 17፡6፤ ሉቃ. 19፡11-14፤ ኤር. 11፡13፤ ሕዝ. 16፡24፡-***

ሀ. ክርስቶስን እንደ ንጉሣችን፣ ጌታችን፣ ራሳችን እና ባላችን ያለማቋረጥ መውሰድ፣ መለማመድ እና መደሰት አለብን፤ ይህም እኛን ለቅዱሳን እና ለአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የበረከት ማስተላለፊያ ለማድረግ እርሱ በረከታችን መሆን ይችል ዘንድ ነው—ማቴ. 2፡2፤ ዮሐ. 1፡49፤ ዕብ. 7፡2፤ ኢሳ. 32፡1-2፤ 33፡22፤ ፊልጵ. 2፡9-11፤ ሮሜ 14፡6-9፤ 2 ቆሮ. 4፡5፤ ቆላ. 2፡19፤ ኤፌ. 1፡22-23፤ 2 ቆሮ. 11፡2-3፤ ሆሴ. 2፡19-20፤ ዘኍ. 6፡23-27፤ መዝ. 128፡5፤ 48፡2።

ለ. ማቴዎስ 1፡1 ክርስቶስ "የዳዊት ልጅ የአብርሃም ልጅ" ስለመሆኑ ይናገራል፡-

1. ዓመፀኞች ስለሆንን፣ ንሥሐ መግባት እና በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ በውስጣችን እና በላያችን ይገዛ ዘንድ ክርስቶስን እንደ ዳዊት ልጅ፣ ማለትም፣ እንደ ባለሥልጣናችን፣ እንደ ሉአላዊው ንጉሣችን መቀበል ያስፈልገናል።
2. ክርስቶስ እንደ ዳዊት ልጅ ከሰለሞን እንደሚልቀው ካለን፣ እንደ አብርሃም ልጅ እንደ እውነተኛው ይስሐቅ ይኖረናል፤ ይህ ማለት ክርስቶስን አብዝተን እንደ ንጉሣችን (የዳዊት ልጅ) በወሰድነው መጠን፤ ይበልጥ በአገዛዙ ሥር እንሆናለን፤ ይበልጥ በአገዛዙ ሥር በሆንን መጠን፣ ይበልጥ እንደ በረከታችን (የአብርሃም ልጅ) እንደሰተዋለን፤ ይህ ሁሉን-እንዳካተተው መንፈስ በሂደት ያለፈውና የተጠናቀቀው የሦስታንዱ አምላክ በረከት ነው—ቁ. 1፤ ገላ. 3፡14፣ 16፣ 29።
3. ይህ ለቅዱሳን መቀጠል (በሕይወት ለማደጋቸው) እና በእምነት ለሆነው ደስታቸው (ለክርስቶስ ድሰታቸው) የበረከት ማስተላለፊያዎች እንድንሆን ያደርገናል፤ ሌሎችን ለመባረክ ተጠርተናል፣ ስለዚህ በረከትን እንወርስ ዘንድ እኛ እንደተባረኩ ሰዎች ሁልጊዜ ሌሎችን መባረክ አለብን—ፊልጵ. 1፡25፤ 1 ጴጥ. 3፡9።

II. **በእግዚአብሔር ንግሥና እና ራስነት ሥር እግዚአብሔር የወሰነውን ሥርዓት ለመጠበቅ እና እስራኤልን ሁሉ ወደ ትክክለኛ ስርአት ለማምጣት እግዚአብሔር ሴት ለወንድ መገዛቷን በተግባር የተለማመደችውን ዲቦራን የእስራኤል ፈራጅ እና በእስራኤል እናት አድርጎ ማስነሣቱ**

ሀ. ናዖድም ከሞተ በኋላ የእስራኤል ልጆች በያሕዌ ፊት እንደ ገና ክፉ ሥራ ሠሩ (4፡1)፣ ስለዚህም ያሕዌ እስራኤልን የሠራዊቱ አለቃ ሲሣራ በሆነው በከነዓን ንጉሥ በኢያቢስ እጅ አሳልፎ ሰጣቸው፤ ዘጠኝ መቶ የብረት ሰረገሎች ነበሩትና ነበሩትና የእስራኤልንም ልጆች ለሃያ ዓመት ያህል እጅግ ያስጨንቃቸው ነበር—ቁ. 2፤ 3።

ለ. በመሣፍንት 4 ጊዜ የእስራኤል ወንዶች እግዚአብሔር-ከወሰነው ከመሪነት አገልግሎታቸው ወድቀው ነበር፤ ይህ እግዚአብሔር ሴትን፣ ዲቦራን የእስራኤል ፈራጅ እንድትሆን በማስነሣቱ ልዩ እና ያልተለመደ ነገር እንዲያደርግ አስገደደው፤ እንዲህ ያለች ሴት መነሣት የእስራኤል አጠቃላይ ሁኔታ ለወጠው—ቁ. 4-5።

ሐ. የእስራኤል ልጆች ወደ ያሕዌ ጮኹ (ቁ. 3)፣ ነቢዩቱ ዲቦራም የእስራኤል ፈራጅ ሆና ተነሣች፤ እርሷም የዲቦራ ዛፍ ከሚባለው ዘንባባ በታች ትቀመጥ ነበር፤ የእስራኤልም ልጆች ወደ እርሷ ለፍርድ ይወጡ ነበር (ቁ. 4-5)።

መ. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተገቢ የሆነች ሴት የምታመለክተው ለእግዚአብሔር የምትገዛ፣ የእግዚአብሔርን ሥርዓት የምትጠብቅ ሴትን ነው፤ ይህ እስራኤል ንጉሷ፣ ጌታዋ፣ ራሷ እና ባሏ በሆነው በእግዚአብሔር ፊት መያዝ የነበረባትን ስፍራ ነው፣ እስራኤል ግን የእግዚአብሔር ሚስት የመሆን ስፍራዋን በመልቀቅ እና በሙቶዎች ለሚቆጠሩ ጣዖታት እርሱን በመተው የእግዚአብሔርን ሥርዓት ጣሰች፤ ይህ እስራኤልን ወደ አሳዛኝ ሁኔታ አመጣት።

1. ሶምሶን ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ በሕይወቱ ዘመን በሙሉ ናዝራዊ ነበረ፤ ናዝራዊ ኃይል ለሚገኝበት ለጌታ ራስነት በመገዛት ውስጥ መቆየት እንደነበረበት በማመልከት ፀጉሩን በረዥሙ ማሳደግ ነበረበት—ዘኁ. 6፡5፤ መሣ. 16፡17፤ 1 ቆሮ. 11፡3-6፣ 10፣ 15።
2. ነገር ግን ደሊላ "ነፍሱ እስክትሞት ድረስ" እስክትጨነቅ በየዕለቱ በቃልዋ አስጨነቀችው፣ የኃይሉን ምሥጢር እንዲነግራትም ነዘነዘችው (መሣ. 16፡16)፤ ከሰይጣን የማዛል ስልቶች የተነሣ፣ ሶምሶን በሰይጣን ወጥመድ ውስጥ ወደቀ፣ ፀጉሩ በደሊላ ተላጨ፣ የናዝራዊ መሰጠቱን፣ ኃይሉን፣ የመቀደስ ምስክርነቱ እና የእግዚአብሔርን መገኘት በማጣት በፍልስጤማውያንም ተማረከ (ዳን. 7፡25)።
3. አማኞች በእግዚአብሔር ለተሾሙ ወኪል ባለሥልጣናት መገዛት የለባቸውም የሚለውን ልዩና የተሳሳተ ትምህርት የሚቀበሉ በዚህ ትምህርት ይበላሻሉ፤ በእኛ ዘንድ (በተለይ ባገቡት እኅቶች ዘንድ ኤፌ. 5፡22-24)፣ የሚገዛ፣ መንፈስ፣ መቆሚያ፣ ድባብ እና ውጥን ሊኖር ያስፈልጋል፤ እንደዚህ አይነት ሰው ከሆናችሁ፣ ለእናንተና ለወደፊታችሁ ትልቅ በረከት ይሆናል።

ሠ. በመሣፍንት 5 ያለውን የዲቦራን መዝሙር በማንበብ፣ በችሎታ፣ በብቃት፣ በጥልቅ እውቀትና በአርቆ አስተዋይነት የተሞላች መሆኗን ማየት እንችላለን፤ ነገር ግን እንደዚህ አይነቷ የላቀች እና ብቃት ያላት ማንነት በጣም የምትገዛ ነበረች፤ እግዚአብሔር መሪ አደረጋት፣ እርሷ ግን ተገቢውን ሥርዓት ጠበቀች ባርቅን እንደ መሸፈኛዋ ወሰደች—4፡6-9፤ ተዛ. 1 ቆሮ. 11፡3-6፣ 10።

ረ. ዲቦራ መሸፈኛዋ የሚሆን ወንድ እንደሚያስፈልጋት ተገነዘበች፤ ጳውሎስ በ 1ኛ ቆሮንቶስ 11፡3 እንደሚናገረው፡- "ነገር ግን የወንድ ሁሉ ራስ ክርስቶስ፣ የሴትም ራስ ወንድ፣ የክርስቶስም ራስ እግዚአብሔር እንደ ሆነ ልታውቁ እወዳለሁ።"

ሰ. ይህች የላቀች፣ ልዩ ሴት ለወንድ መገዛቷን በተግባር ለመለማመድ ቅድሚያውን ስትወስድ፣ መላው አገር ወደ ላቀና ተገቢ ሥርዓት መጣ፤ ሁሉም መሪዎች ቅድሚያውን ወሰዱ፣ ሕዝቡም ሁሉ ተከተሉ፣ ሠራዊቱም ተሠራ፤ ሁሉም ሰው በያሕዌ ፊት ወዳለው ወደራሱ ወይም ወደራሷ ተገቢ ስፍራ ተመለሱ።

ሸ. ስለዚህ ዲቦራ በመዝሙሯ "በእስራኤል ውስጥ መሪዎች ስለ መሩ፥ ሕዝቡም ነፍሳቸውን በፈቃዳቸው ስለ ሰጡ፥ እግዚአብሔርን አመስግኑ...በዚያ ጊዜ የቀሩት ወደ ኃያላኑና ወደ ሕዝቡ ወረዱ፤ እግዚአብሔርም ስለ እኔ በኃያላን ላይ ወረደ"—መሣ. 5፡2፣ 13።

ቀ. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የመጀመሪያውና ታላቁ የእኅቶች አገልግሎት መገዛት ነው፤ እኅቶች ይህንን ትምህርት መማር ከቻሉ፣ ቤተ ክርስቲያን ጠንካራ፣ የበለጠገችና የታደሰች ትሆናለች፡-

1. የሚገዙ ለመሆን የሕይወት አቅርቦትን፣ የጸጋ ድሰታን፣ የመስቀሉ መሥራትን እና የእኔነት መካድን ይጠይቃል።
2. በክርስቶስ የተሞሉ በመገዛት የተሞሉ ናቸው፤ በሕይወት ዘመኑ ሁሉ የሚገዛ የነበረው ጌታ፣ የራሱን የመገዛትና የመታዘዝ ሕይወት ሰጥቶናል—ፊልጵ. 2፡5-11፤ ዕብ. 5፡7-9።
3. አንድ እኅት አንድ ወንድምን ማግባቷ ራሷን ለመስጠት እና "ለመገዛት ፈቃደኛ ነኝ" ለማለት ፈቃደኛ ናት ማለት ነው። አንድ እኅት ልታገባው ላሰበችው ሰው ለመገዛት ፈጽሞ ፈልጋ የማታውቅ ከሆነ፣ ሚስቱ መሆን የለባትም፣ እርሱን ማግባትም የለባትም—ኤፌ. 5፡22-23፤ 1 ጴጥ. 3፡1-6።

## III. ዲቦራ የተነሣችው እንደ የእስራኤል ፈራጅ ብቻ ሳይሆን በእስራኤል እንዳለች እናትም ነበር—መሣ. 5፡7፡-

ሀ. የቤተ ክርስቲያን ሕይወት በተግባራዊ ደረጃ ከፍተኛ ጫፍ ሲደርስ፣ በእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን እውነተኛ እናቶች ሊኖሩ ይገባል፤ በሮሜ 16፡13 ጳውሎስ "በጌታ ሆኖ ለታወቀ ለሩፎን ለእኔና ለእርሱም እናት ሰላምታ አቅርቡልኝ" ይላል፡-

1. ሐዋርያው ጳውሎስ እናት አስፈልጎት ነበር፤ እነርሱን ለመንከባከብ እናት የሆነች እኅት ከሌለች፣ ለጌታ አገልግሎት ሸክም የሚሸከሙ ሁሉ ሀዘንተኞች ይሆኑ ነበር፤ እንክብካቤአቸው እውነተኛ ምግባችን እና እውነተኛ ጥበቃችን የሆነ የመንፈሳዊ እናቶች እንክብካቤ ሁላችንም ያስፈልገናል።
2. ጳውሎስ መንፈሳዊ እናት ያለው መሆኑ የሚያመለክተው በሮሜ ባለች ቤተ ክርስቲያን የነበሩ ቅዱሳን በክርስቶስ መሰቀልና ትንሣኤ በኩል የሕይወት ሽግግር እንደነበራቸው ነው፤ የሕይወት ሽግግር እንዲኖረን ምርጡ መንገድ ሁሉን-ያካተተው ክርስቶስን እና እርሱም እንደተሰቀለ እንጂ ሌላ ነገር ላለማወቅ የቆረጠውን የጳውሎስን ምሳሌ በመከተል ነው—1 ቆሮ. 2፡2።

ለ. የዮሐንስ ወንጌል በሕይወት ላይ፣ በተፈጥሮአዊው ሕይወት ላይ ሳይሆን በተሸጋገረው እና በተለወጠው ሕይወት ላይ የሚያተኩር መጽሐፍ ነው፤ በመጀመሪያ፣ ዮሐንስ የማርያም ልጅ አልነበረም፣ ማርያምም የዮሐንስ እናት አልነበረችም፣ ነገር ግን በክርስቶስ ሕይወት-የሚለቅ ሞት እና ሕይወት-የሚያድል ትንሣኤ፣ እንዲሁም ከእነርሱ ጋር ባለው የሕይወት

ጥምረት፣ የተወደደው ደቀ መዝሙሩ ከእርሱ ጋር አንድ መሆን እና የእናቱ ልጅ መሆን ችሏል፣ እርሷም የተወደደው ደቀ መዝሙሩ እናት መሆን ችላለች—19፡26-27።

ሐ. የመጀመሪያው ግንኙነታችን በሥጋ ነው፣ ሁለተኛው ግን በመንፈስ፣ ማለትም፣ በተሸጋገረው ሕይወት ነው፤ ሁለተኛው ውልደት ስላለን (3፡6) ከእውነተኛ እኅቶችና ከእውነተኛ እናቶች ጋር በእርግጥ ሁለተኛው ግንኙነት፣ ሁለተኛው ቤተሰባዊ ግንኙነት አለን።

መ. እኅቶች እውነተኛ እናቶች ለመሆን የጸሎትና የእምነት መንፈሳቸውን ካንቀሳቀሱ (2 ቆሮ. 4፡13)፣ ምን ያህል ራስ ወዳዶች እንደሆኑና ምን ያህል በራሳቸው ውስጥ እንደሆኑ ይገነዘባሉ፤ በመንፈስ የሆኑ መልካም ልጆችን ማግኘት ፈጽሞ ያጋልጣቸዋል፤ በተጨማሪም፣ እኅቶች የተወሰኑ መንፈሳዊ ልጆችን በመንከባከብ በሕይወት ያድጋሉ ይበስሉማል።

ሠ. እኅቶች ጌታን ከወደዱና በጌታ ምለሳ ላለው የቤተ ክርስቲያን ሕይወት ለመሆን ከቆረጡ፣ እውነተኛዋ ሆስፒታል በሆነችው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ራሳቸውን በሞግዚትነት የሚያገለግሉ፣ የቤተ ክርስቲያን ሞግዚቶች አድርገው መቁጠር አለባቸው፤ ሁሉም እኅቶች በፀሎት የሚያገለግሉ እኅቶች እና በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እና በቤተ ክርስቲያን ሕይወታቸው የተቸገሩትን እና ወጣቶችን ለመርዳት እጅግ በላቀ የፍቅር መንገድ አፍቃሪ እናቶች መሆን ያስፈልጋቸዋል፤ ይህ በረከትን፣ እድገትን፣ መንፈሳዊነትን እና እውነተኛውን የጌታ ድሰታ የመቀበያ ምርጡ መንገድ ነው—ሮሜ 16፡1-2፣ 13፤ ኢሳ. 66፡12-13፤ 1 ቆሮ. 12፡31፣ 13፡4-7።

**IV. መጽሐፍ ቅዱስ በዚያን ጊዜ በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል "ታላቅ የልብ ውሳኔ" እና "ታላቅ የልብ ምርምር" ነበረ ይላል—*መሣ.* 5፡15-16፡-**

ሀ. ታላቅ ውሳኔ ማድረግ ጽኑ ውሳኔ ማድረግ ነው፣ ታላቅ ምርምር ማድረግ ለጌታ ለመኖርና ጌታን ለመኖር የጊዜው በሆነው ምለሳው በአካሉ መገንባት፣ በሙሽራው መዘጋጀት፣ በመንግሥቱ በመገለጡ መምጣት እቅድ መንደፍ ነው—2 ቆሮ. 5፡14-15፤ ሮሜ 14፡7-9፤ ራእ. 19፡7-9።

ለ. ወንድም ሊ በ1943 በጃፓን ወታደር-ፖሊሶች በመጨቆን ሂደት ውስጥ እያሉ፣ ጌታ ንጋትን፣ በማለዳ እንዳለ ንጋት፣ በጣም ብሩህ፣ በጣም ቀጥ ካለ፣ ያለገደብ ከሚዘረጋ ሰፊ አውራ ጎዳና መንገድ ጋር ያዩበትን ሕልም ሰጣቸው፤ ይህ የጌታ ምለሳ ሰፊው አውራ ጎዳና፣ የምትወጣዋ ፀሐይ፣ ገደብ የሌለው ወደፊት ነው—ተዛ. ምሳ. 4፡18።

ሐ. ዲቦራ ክቡር በሆነ መንገድ በሚደመድመው በመዝሙሯ መጨረሻ "ወዳጆችህ ግን ፀሐይ በኃይሉ በወጣ ጊዜ እንደሚሆን፣ እንዲሁ ይሁኑ" እንዳለቻቸው ሰዎች አይነት ለመሆን መሻትና መጸለይ ያስፈልገናል—መሣ. 5፡31፡-

1. ፀሐይ በኃይሉ መውጣቱ ማለት፣ ብሩህ፣ ደማቅ እና የከበረ በሆነ መልኩ ያበራል ማለት ነው፤ ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ቁርጠኛ ውሳኔዎችን፣ ምርምሮችን እና እንደፀሐይ ለማብራት መውጣትን ቢለማመዱ፣ በእርግጠኝነት ጌታን እንደ ድላቸው ይደሰታሉ።
2. እንደ ጽድቅ ፀሐይ በሚፈውሰው ክርስቶስ እንደገና የተቀናበሩ ድል-ነሺዎች በአባታቸው መንግሥት እንደ ፀሐይ ያበራሉ—ሚል. 4፡2፤ ሉቃ. 1፡78-79፤ ማቴ. 13፡43።

*© 2021 Living Stream Ministry*